ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

ቁጥር
Ref. No 24/ከመ21/3/2
ቀን
Date 19/06/2012

# ለ ሚ መ ለ ከ ተ ው ሁ ሉ

ጉዳዩ:- <u>የዕጽዋት ዘር ፖሊሲ መጽደቁን ስለማሳወቅ</u>

የግብርና ሚኒስቴር ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ አገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርሙን ተከትሎ እየታየ ያለውን ምጣኔ ሃብታዊ መነቃቃት በዘር ንዑስ ዘርፉም ለማስቀጠል እንዲቻልና ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ ተዋንያን በዕጽዋት ዘር ዘርፉ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የአገራችንን የዘርፉን ቀጣይ አቅጣጫ የሚያመላክት የፖሊሲ አቋም እንዲኖር በመታመኑ የዕጽዋት ዘር ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊነት ታምኖበት ሲሰራበት ቆይቷል።

የግብርና ሚኒስቴርም ከሚኒስትሮች ምክር ቤት በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የሚኒስቴሩ ማናጅመንት በወሰነው መሰረት የቀረበውን የዕፅዋት ዘር ፖሊሲ የሚኒስቴሩ ፖሊሲ አድርጎ ያጸደቀው መሆኑን እየገለጽኩ በዕፅዋት ዘር ንዑስ ዘርፉ የሚረቀቁ የህግ ማዕቀፎችና የሚካሄዱ የልማት ተግባራት በዚህ ፖሊሲ መሰረት የተቃኙ እንዲሆኑ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር!

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ዑመር ሁሴን
ሚኒስትር

# ግብርና ሚኒስቴር

## ብሔራዊ የዕፅዋት ዘር ፖሊሲ

የካቲት 2012 ዓ/ም


The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Agric

## ማውጫ


መግቢያ ........ 3

ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ ........ 4

1. ራዕይ ........ 4

2. ተልዕኮ ........ 4

3. የፖሊሲው አስፈላጊነት ........ 4

4. የፖሊሲው ዓላማዎች ........ 5

5. የፖሊሲው መሰረታዊ እሳቤዎች ........ 6

6. የፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች ........ 6

7. መርሆዎች ........ 7

8. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች ........ 7

9. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ማዕቀፍ ........ 7

10. የፖሊሲው አድማስ ወይም ወሰን ........ 8

ክፍል ሁለት፡- የፖሊሲው ይዘት ........ 9

11. የዕፅዋት ዝርያ ማፍለቅ ........ 9

12. የዝርያ ለቀቃ እና አመዘጋገብ ........ 11

13. የዕፅዋት ዝርያ አዳቃዮች እና የአርሶ /አርብቶአደሮች መብት ጥበቃ ........ 13

14. የዕፅዋት ዘር ማምረትና ማዘጋጀት ........ 15

15. የዕጽዋት ዘር ግብይትና ሥርጭት ........ 17

16. የዕፅዋት ዘር ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለ መላክ ........ 20

17. የዕፅዋት ዘር ጥራትን ስለማረጋገጥ ........ 21

18. የዕፅዋት ዘር ኳራንቲን ........ 23

19. የዕፅዋት ዘር ብዝኃ ሕይወት ........ 24




የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agric...

20. የዕፅዋት ዘር ሥርዓት አደረጃጀት እና አመራር ..... 26

ክፍል ሦስት፡- ልዩ ልዩ ጉዳዮች ..... 27

21. የፖሊሲው አጭር መግለጫ ..... 27

22. የፖሊሲ ክትትል፣ የግምገማና የክለሳ ስርዓት ..... 27

23. የፖሊሲው ስርጭት ..... 28

24. ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ ..... 28

ዕዝል አንድ፡- የቃላትና ፅንሰ ሀሳብ ፍቺ ..... 29

## መግቢያ

መንግሥት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኤኮኖሚ ልማት ለማስመዝገብና ሁሉም ዜጋ እንደ የተሳትፎው ከኢኮኖሚው ተጠቃሚ የሚያደርግ የገጠር ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ስልት ነድፎ በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት በግብርናው ዘርፍ እየተመዘገበ ያለውን እድገት ፈጣንነትና ቀጣይነት ለማረጋገጥ ውጤታማ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ እንዲሆኑ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህንን ለመፈፀም የሚያስችለው የመጀመሪያው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማጠናቀቅ የሁለተኛውን ዘመን በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በሁለተኛው ዘመን ዕቅድ እንደተመለከተው ግብርናውን ወደ ከፍተኛ የምርትና ምርታማነት ደረጃ እንዲሸጋገር ይጠበቃል፡፡ በሰብል የምርታማነትን ዕድገት እውን ለማድረግ ደግሞ የዘር ሥርዓቱን በአግባቡ መምራት፣ ማደራጀትና አቅም መገንባት በአጠቃላይ ኢንዱስትሪውን ማዘመን ይጠይቃል፡፡

በሌላ በኩል አዳዲስ ዝርያ ማፍለቅና ማጎልበት ረዥም ጊዜና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ በመሆኑ በፍጥነት ወደ ምርት ሊገቡ የሚችሉ የውጭ ዝርያዎች ወደ አገር ውስጥ አስገብቶ በማላመድ መጠቀም እንዲቻል ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚጠይቁትን ግዴታዎች በማሟላት ተጠቃሚ ለመሆን የመንግሥትን አቋም በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ የተሻሻለ ዝርያ ዘር ማምረት የብዙ ባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ስለሚጠይቅ የእነዚህን ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ኃላፊነት ምን መሆን እንዳለበት በፖሊሲ በግልጽ ሲቀመጥ ባለድርሻ አካላቱ በዘርፉ ላይ የሚኖራቸውን ሚና አውቀው ተሳትፎ ለማደረግ መወሰን ያስችላቸዋል፡፡

የዘር ዋስትናንና ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቋቋም፣ የባዮቴክኖሎጂና የግሎባላይዜሽን ተጠቃሚነትን በአግባቡ ለማረጋገጥ፣ የስርዓተ ፆታንና የስነ-ምግብንና በአጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ የሚጠበቀውን ግብ ለማሳካት የሚያስችል አመቺ የፖሊሲ ምህዳር ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡ የአገራችንን የዘር ኢንዱስትሪውን ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመቃኘት በዘርፉ ብቁ ተወዳዳሪ ሊያደርገን የሚችል እና ከሁሉም በላይ ደግሞ አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚፈልገውን ዘር በመጠን፣ በጥራት ፣ በገበያ ተወዳዳሪነት በሚመራ

ዋጋና በወቅቱ በተቀላጠፈ ሁኔታ ማቅረብ የሚያስችል አገራዊ የዘር ፖሊሲ በግልፅ ማስቀመጥ አስፈልጓል።

የፖሊሲው ቀረፃ በዋናነት በአገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ የሚመሠረት ቢሆንም የዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች በመገምገምና በመተንተን ጠቃሚ ልምድ እንዲካተትበት ጥረት ተደርጓል። ከዚህ አኳያም የተመረጡ የአህጉራችን አገሮች፣ ቀጠናዊ ስብስቦች እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተዳሰዋል። አገሪቱ በዘር ኢንዱስትሪው ግንባታ ሂደትዋ ያስመዘገበቻቸውና ያካበተቻቸው ተሞክሮዎች፣ ንዑስ ዘርፉ የገጠሙት ተግዳሮቶችና አሁን የሚገኝበትንም ደረጃ ከዓለም አቀፍ አሠራሮች ጋር በማነፃፀር በፖሊሲው ውስጥ የሚካተቱትን ጉዳዮች ለመለየት የፖሊሲ ቀረፃ መመርያዎችን መሠረት በማደረግ ረቂቅ ሰነዱ ተዘጋጅቷል።

## ክፍል አንድ፡ አጠቃላይ

### 1. ራዕይ

የአርሶ/ከፊል/አርብቶ አደሩንና የአልሚ ባሀብቱን የዕፅዋት ዘር ተጠቃሚነት ያረጋገጠ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ በአገሪቱ ተገንብቶ ማየት ነው።

### 2. ተልዕኮ

ዘመናዊ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ በመገንባት የዕፅዋት ዘር ተጠቃሚው የሚፈልገውን ዘር በጥራት፣ በመጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋ በሚፈለግበት ስፍራና ጊዜ እንዲቀርብ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ማሳደግና በዓለም የዕፅዋት ዘር ገበያ መሳተፍ ነው።

### 3. የፖሊሲው አስፈላጊነት

የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥን መሰረት ያደረገ ስትራቴጂካዊ የምግብና የመኖ ምርቶች በማምረት በማንኛውም ወቅት የዕፅዋት ዘር ዋስትናን እና ሉዓላዊነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣

ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚያስፈልጉትን ጥሬ ዕቃዎች ለማምረት የሚያስፈልግ የዕፅዋት ዘር በጥራት፣በዓይነት፣በመጠንና በጊዜ ያለማቋረጥ በተከታታይ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ኢንቨስትመንትን በመሳብ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ከማስቀረት ወደ ማመንጨት ለመሸጋገር እና የሥራ ዕድል መፍጠር ላይ የዘርፉን ድርሻ ለማሳደግ ከሁሉም በላይ ደግሞ የተሻሻለ የዕፅዋት ዝርያ ዘር ተጠቃሚው በሚፈልገው ልክ ማሟላት አስፈላጊነቱ እየጎላ በመምጣቱ፤

አገሪቱ በአህጉራዊ የጋራ ገበያዎች አባል መሆኗ እና በዓለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ለምታደርገው ጥረትና በቀጣይም በውጭ ገበያ በዘርፉ ተጠቃሚነቷን ለማረጋገጥ ግልጽ የዕጽዋት ዘር እድገት አቅጣጫ መንደፍ አስፈላጊ እየሆነ መምጣቱ፤

የዕፅዋት ዘር ሥርዓቱን አደረጃጀትና አመራር በማዘመን የዘርፉን ተጠቃሚነት በማሳደግ የዘርፉን ባለድርሻ አካላት እርካታ ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በአገሪቱና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ዕድገትና ለውጥ እየታየ ቢሆንም እስከ አሁን አገሪቱ ራሱን የቻለ የፀደቀ የዕፅዋት ዘር ፖሊሲ የሌላት በመሆኑ ፖሊሲ መቅረፅ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 4. የፖሊሲው ዓላማዎች

የዚህ ፖሊሲ ዋና ዓላማ የአገሪቱን የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ በማዘመንና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን በማስፈን የዕፅዋት ዘር ዋስትናን ከማረጋገጥ አልፎ በውጭ ገበያ የዘርፉን እድል መጠቀም ነው። በተጨማሪም የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፤

4.1. የብዝኃ ሕይወት ሃብትን፣ የዕፅዋት አዳቃዮችን፣ የአርሶ/አርብቶ አደሮችን እና የማህበረሰብ እውቀት መብትን ለማስጠበቅና የአርሶ/አርብቶ አደሩ ዝርያ የሚመዘገብበት ሥርዓት ለመዘርጋት፤

4.2. የዕፅዋት ዘር ዋስትናንና ሉአላዊነትን ለማስከበር እና የዘር አቅርቦት በጥራት፣ በዓይነት፣ በመጠን በዘላቂነት በማረጋገጥ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤

4.3. የአገሪቱ የዕፅዋት ዘር እንዱስትሪውን ለማዘመንና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማስፈን ቴክኖሎጂና ኢንቨስትመንት በመሳብ ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣

4.4. በዓለም ገበያ ተሳታፊና ተወዳዳሪ የሚያደርግ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተለይ የግሉን ዘርፍ የሚያበረታታ የዘር ኢንዱስትሪ መገንባት፤

## 5. የፖሊሲው መሰረታዊ እሳቤዎች

መንግስት ለግብርናው እድገት ያለውን አስተዋፅኦ በመንገዘብ

5.1. ለዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ትኩረት ይሰጣል፤

5.2. የዘር ኢንዱስትሪ በነፃ ገበያ መርህ ይመራል ፤

5.3. ለዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኢንቨስተመንትን የሚያበረታታ አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል፤

5.4. አገሪቱ በአህጉርና አለም አቀፍ የንግድ ስርዓት ጉልህ ተሳትፎ ታደርጋለች፤

## 6. የፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉትን ግቦች እንዲያሳካ ይጠበቃል፡-

6.1. የተቀላጠፈና የተቀናጀ አገልግሎት መስጠት የሚችል የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ አሰራር ስርዓት ይገነባል፤

6.2. የዕፅዋት ዘር ዋስትናና ሉዓላዊነት ይረጋገጣል፤

6.3. ከፍተኛ ምርታማነትና የገበያ ፍላጎትን የሚያሟሉ ዝርያዎችን በተከታታይ ይወጣሉ፤

6.4. ተጠቃሚው የሚፈለገውን ዘር በትውልድ፣ በጥራት፣ በመጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በተፈለገበት ስፍራና ጊዜ ያገኛል፤

6.5. አገሪቱ ኢንቨስትመንትንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማበረታታት በዓለም የዕፅዋት ዘር ገበያ ተወዳዳሪ በመሆን የውጭ ምንዛሪ ያድጋል፤

## 7. መርሆዎች

ይህ የዕፅዋት ዘር ፖሊሲ በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ነው፤

7.1. የአገር ውስጥ ብዝሀ ዘር የማህረሰብና የመንግስት ሀብት ነው፤

7.2. ውጤታማ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ተደራሽነትን ያረጋግጣል፤

7.3. የዕፅዋት ዘር ስርዓቱ በነፃ የገበያ ውድድር ይመራል፤

7.4. የዕፅዋት ዘር ዋስትናንና ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ ቅድሚያ ትኩረት ይሰጠዋል፤

7.5. አገሪቱ የተቀበለቻቸውን የዓለምና አህጉር አቀፍ ስምምነቶችን ታከብራለች፤

7.6. የዕፅዋት ዘር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና ትብብር ይሰራሉ።

## 8. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

የዘር ፖሊሲውን ለማስፈፀም ከአደረጃጀት ጀምሮ የዘር ስትራቴጂ ይነደፋል፤ አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎች ይዘጋጃሉ፤ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ተነድፈው ይተገበራሉ።

## 9. የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ማዕቀፍ

ፖሊሲው የሚከተሉት ዝርዝር ማዕቀፎች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

9.1. መንግስት የዘር አመራርን በተመለከተ ኃላፊነት የተሰጠውን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የሚያማክር ከባለድርሻ አካላት የተውጣጣ ምክር ቤት በህግ ያቋቁማል፤

9.2. መንግስት የዘር ኢንዱስትሪውን በበላይነት እንዲመራ ግብርና ሚኒስቴርን ይሰይማል፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

9.3. ምርምር ነክ ተግባራት መንግስት በተሰየመው በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት አመራር (የክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩቶች፤ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ ስኳር ኮርፖሬሽን፤ ግብርና ምርምር የሚያካሂዱ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት፣ የደንና አካባቢ ምርምር ኢንስቲትዩት፣የግል ምርምር ኩባንያዎች) ይካሄዳል፤

9.4. ብዛ ዘር ጥበቃና አጠቃቀምን በተመለከተ መንግስት በሰየመው በኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት ይካሄዳል፤

9.5. በዘር ንግድ ላይ ለሚሰማራ ማንኛዉም አካል ፍቃድ አሰጣጥን የንግድና ኢንዱስተሪ ሚ/ር በኃላፊነት ይመራል፤

9.6. የዘር ንግዱን በተመለከተ እንደ ሌሎች ምርቶች ሁሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኃላፊነት ይመራል፤

9.7. የዘር ጥራት ማረጋገጥን በተመለከተ የግብርና ሚኒስቴርና ጉዳዩ በሚመለከተው አግባብ ባለው የክልሉ ባለስልጣን ኃላፊነት ይመራል፤

9.8. የደረጃዎች ኤጀንሲ ያፀደቃቸው ደረጃዎች በሁሉም ክልሎች ተፈፃሚነት አለው፤

9.9. የዘር እንዱስትሪዉን ለማሳደግ በዘር እሴት ሰንሰለት ውስጥ የመንግስትና የግል ባለሀብቶች (የሀብረት ስራ ማህበራትን ጨምሮ) እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

## 10. የፖሊሲው አድማስ ወይም ወሰን

በአገር አቀፍ ሆነ በዓለም አቀፍ ሕጎች እንዳይመረቱ ከተከለከሉት በስተቀር ይህ ፖሊሲ ማንኛውንም የዕፅዋት ዘር ተብሎ የተሰየመ በመባዛት ራሱን መተካት የሚችል ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤት ሁሉ ያካትታል፡፡ በዕፅዋቱ ልዩ ባሕሪይ ምክንያት በዚህ ፖሊሲ የተገለፁትን መሠረታዊ ጉዳዮች ሳይቃረን የሚመለከተው አካል ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያካትት ፖሊሲ የመቅረጽ ኃላፊነቱን አይገድብም፡፡

## ክፍል ሁለት፡- የፖሊሲው ይዘት

### 11. የዕፅዋት ዝርያ ማፍለቅ

ዝርያ ማፍለቅ ማለት ብዛ ዘርን በመጠቀም በምርታማነትና ከባቢያዊ ጫና የመቋቋም አቅም ወይም የኢንዱስትሪና የገበያ ጥራት ፍላጎት የሚያሟላ የተሻለ ድቃይና ድቃይ ያልሆነ ዝርያን በመረጣ፣ በማዳቀል እና ሌሎች ዘመናዊ ዘዴዎች በመጠቀም በተለያዩ ስነ ምህዳሮች ወይም ለተለየ አካባቢ በመሞከር መለየት ማለት ነው፡፡ በሌላው ዓለም ዝርያ ማፍለቅ በአገራዊና ዓለም አቀፍ ምርምር ተቋማት፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና በግል ዘር አፍላቂ ኩባንያዎች የሚከናወን ቢሆንም በአገራችን የዝርያ ማፍለቅ ሥርዓቱ አሁን ያለበት ደረጃ ከዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ቁመና የሚገኝ አይደለም፡፡ በመሆኑም የምርታማነት፣ በሽታና ከባቢያዊ ጫና (በሽታ፣ ተባይ፣ ጨዋማነት፣ አሲዳማነት፣ ሙቀት፣ ውርጭ ወ.ዘ.ተ ) የመቋቋም አቅም ያላቸው፣ የጥራት ደረጃና የገበያ አይነቶችን (Market Class) የሚያሟሉ እና በሰፊ የግብርና ስነ-ምህዳር የሚላመዱ ዝርያዎችን በበቂ ሁኔታ ማውጣት አልተቻለም፡፡ በዝርያ ማፍለቅ የሚታዩ ተግዳሮቶች፣ ማነቆዎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

11.1. በዝርያ ማፍለቅ የሚታዩ ተግዳሮቶች እና ማነቆዎች፡-

11.1.1. የምርምር ስርዓቱን ለዝርያ ማፍለቅ እና ማደስ በበቂ ሰው ሃብት ልማት፣ አስፈላጊ በሆኑ መሰረተ ልማቶችና (የመስኖ፣ የቤተ ሙከራ፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ መጋዘኖች፣ ቀዝቃዛ ቤቶች)፣ በሎጅስቲክስ አቅርቦት እና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ያለበት የእድገት ደረጃ ውስን መሆን፤

11.1.2. የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር አዳቃዮችን በዝርያ ማፍለቅና ማሻሻል እንዲሰማሩ የሚያስችል ሥርዓት ያለመኖር፤

11.1.3. ለአገር በቀል ብዛ ዘር (Indegenious Germplasm) ዝርያ ማፍለቅና ማሻሻል ላይ የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ በቂ ዝርያ አለመቅረቡ፡፡

11.1.4. የአርሶ/አርብቶ አደሩን ዝርያዎች ለማስመዝገብ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ያለመኖር፤

11.2. መንግስት በዝርያ ማፍለቅና ማደስ ላይ የሚታዩትን ቁልፍ ችግሮች ለመፍታት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፤

11.2.1. የዝርያ ማፍለቅ መሰረት የሆነውን የብዙ-ዘር ምርምር የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፤

11.2.2. መንግስት የስትራቴጂካዊ ሰብሎችን ዘር ሉዓላዊነትን ተግባራዊ ለማድረግ የዝርያ ማፍለቅና ማደስ አገራዊ አቅምን ይገነባል፤

11.2.3. መንግስት ለዝርያ ማፍለቅ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች፣ የሰው ሃብት ልማትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚስፋፋበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱም የቀጥታ ድጋፍ ያደርጋል፤

11.2.4. በምርምር ሥራ እንዲሰማሩ እውቅና የተሰጣቸውን የአገር ውስጥና የውጭ አገር የግል ተቋማትን በተመረጡ ሰብሎች ላይ በዝርያ ማፍለቅና ማጎልበት ሥራ እንዲሰማሩ የሚፈቅድ እና የሚያበረታታ ሥርዓት ይመቻቻል፤

11.2.5. የዝርያ ማፍለቅና ማደስ ሥራ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ችግር የሚፈታ፣ሥነ ምህዳርን መሰረት ያደረገ፣ገበያ ተኮር እና ተወዳዳሪ የሆነ የአገር ውስጥና የዓለም ገበያን እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፍላጎትን እንዲያሟላ ይደረጋል፤

11.2.6. የግብርና ምርምር ተቋማት የሚያፈልቁትንና የሚያጎለበቱትን አዳዲስ ዝርያዎች ገበያ ላይ ለማዋል እና የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከዘር አምራች ተቋማት ጋር የዝርያ መጠቀም ልዩ መብትን (exclusive use right) በማስተላለፍ እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

11.2.7. ከአገር ውስጥ የሚገኝና ለዝርያ ማፍለቅ የሚውል ብዛ ዘር ለመንግስት እና ለአገር ውስጥ የግል አዳቃዮች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፤

11.2.8. ከአገር ውስጥ የሚገኝን ብዛ-ዘር ተጠቅመው ዝርያ የሚያፈልቁ የውጭ አገር ኩባንያዎች በአገሪቱ ሕጎች እና በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፤

11.2.9. የዝርያና የእውቀት ባለመብቶች ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ብሔራዊ የዘረ-መል ፈንድ ይቋቋማል፤



የኢትዮጵያ ፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

11.2.10. የአርሶ/አርብቶ አደሩ ወይም የማህበረሰብ ወይም የአካባቢ ዝርያዎች እንዲመዘገቡ አስፈላጊው የባሕርይ ልየታ ምርምር እንዲካሄድባቸው የድጋፍ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

11.2.11. የሰብል ዝርያዎች ሲጎለብቱ የሴቶችን ጉልበት እና ጊዜ በሚቆጥብ እና ተጠቃሚነታቸውን በሚረጋገጥበት መንገድ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 12. የዝርያ ለቀቃ እና አመዘጋገብ

የሰብል ዝርያ ማለት አንድ ወጥ የሆነ የማይዋዥቅ ባህሪ ያለውና በአንድ አይነቱ (Species) ውስጥ ካሉ ሌሎች ዝርያዎች የተለየ በቀላሉ ሊለይ የሚችል (Morphological)፣ ባዮኬሚካል (Quality Traits) ወይም ሞለኪውላር (Molecular Marker or DNA Finger Print) መለያ ባህሪ ያለው ነው፡፡ አንድ የሰብል ዝርያ ዘሩ በሰፊው ተመርቶ ወደ ምርት ከመግባቱ በፊት የዝርያውን ጠቀሜታና የአግሮኖሚ ብቃቱን ለማወቅ (Value for Cultivation and Use) በብሔራዊ የዝርያ ግምገማ ሙከራ (National Performance Test, NPT) ተገምግሞ ተቀባይነት ሲያገኝ በብሄራዊ የዝርያ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡ የተለቀቀ ዝርያ የባለቤትነት መብት ጥበቃ እንዲደረግለት ጥያቄ ሲቀርብ የተለየ (Distinict)፣ ወጥነት ያለው (Uniform) የማይዋዥቅ (Stable) ሙከራ (DUS-test) ተካሂዶ መስፈርቶችን ሲያሟላ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

የዝርያ ለቀቃና ምዝገባ ሥራ የሚከናወነው ዝርያው ጥቅም ላይ እንዲውል እውቅና ለመስጠት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ የስነ ምህዳር ቀጣናዎች ለተወሰኑ ወቅቶች የመስክ ሙከራዎች ይደረጋል፡፡ በብዙ አገሮች ዝርያ ለቀቃና ምዝገባ እንደ የሰብሉ ዓይነት አስገዳጅ ወይም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው አገሮች የዝርያ ብቃት ግምገማ ተግባራት የሚከናወነው ራሱን በቻለ ተቋም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለሁሉም የሰብል ዓይነቶች ዝርያ ለቀቃና ምዝገባ አስገዳጅ ሲሆን ለዝርያ ግምገማ የሚሆነው ሙከራ የሚከናወነው ዝርያ በሚያፈልቀው ተቋም ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ ውጤታማ፣ አሳታፊና ታአማኒ የሆነ የዝርያ ለቀቃ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ቀጥለው ሰፍረዋል፡፡

12.1.በዝርያ ለቀቃና አመዘጋገብ የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች፡-

12.1.1.የዕፅዋት ዝርያ ከመለቀቁ በፊት የሚደረጉ የብሔራዊ ዝርያ ብቃት ግምገማ (National Performance Trial) እና የዝርያ ባሕርይ ልየታ (ዲ.ዩ.ኤስ) ሥራዎች ዝርያ የሚያፈልቁና የሚያጎለብቱ አካላትን በገለልተኝነት ሊመራ በሚችል ተቋም አለመካሄዱ፤

12.1.2.የዝርያ ለቀቃ ሂደቱ በተጠናከረ መልኩ የአገር ውስጥና የውጭ ገበያ ፍላጎትን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ የሚለቀቁ ዝርያዎች በገበያ ተፈላጊ እና ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ማድረጉ፤

12.1.3. እንደ ሰብሉ ባሕርይ በአገር ውስጥ ዝርያው ሳይመዘገብ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ አገር ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያደርግ ሥርዓት ያለመኖር፤

12.1.4. አዲስ ዝርያ ሲመዘገብ ዝርያውን የሚወክል የዘር ናሙና (Authetic Sample) እና ዲኤን ኤ አሻራ (DNA Finger Printing) ዝርያ ለቀቃና ምዝገባን በተመለከተ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንዲቀመጥ የሚያደርግ ሥርዓት አለመኖሩ፤

12.1.5. የተመዘገበና በምርት ውስጥ ያለ ዝርያ የምርታማነትና የበሽታ መቋቋም አቅሙ እየደከመ ሲመጣ ከምርት ውጭ የሚሆንበት አሰራር አለመኖር፤

12.2. መንግስት በዝርያ ለቀቃና አመዘጋገብ የሚታዩ ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤

12.2.1.የዝርያ ለቀቃና ምዝገባ ሂደት ዓለም አቀፋዊ አሰራሮች መሰረት ባደረገ፣ የመንግስትንና የግል ዝርያ አልሚ ባለድርሻዎችን በእኩልነት ሊያስተዳድር በሚችል ራሱን ችሎ በተደራጀ መንግስታዊ ተቋም እንዲመራ ይደረጋል፡፡

12.2.2.የሰብል ዝርያዎች ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ እንዲለቀቁ የሚያስገድድ የብቃት ማረጋገጫ ሙከራ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

12.2.3.ለተመረጡ ሰብሎች አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪው አካል የዝርያ ብቃት ማረጋገጥ ሙከራ መስራት ሳያስፈልግ የዝርያው ባለቤት በሚያቀርበው



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

የአገር ውስጥ የማላመድ ሙከራ ውጤት መሰረት ጥቅም ላይ የሚውሉበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

12.2.4.ዝርያው ለውጭ ገበያ ብቻ የሚፈለግ ከሆነ ሳይመዘገብ በአገር ውስጥ ተባዝቶ ቀጥታ ወደ ውጭ የሚላክበት ሥርዓት ይዘረጋል።

12.2.5. የተለቀቀ ወይም የተመዘገበ ዝርያ ምርታማነቱ ሲቀንስ ወይም ሲለቀቅ የነበረውን ባሕርይ እንደለወጠ ሲታመን ከብሔራዊ የዝርያ መዝገቡ እንዲሰረዝና በሰው፣ በእንስሳት፣ በእጽዋት ጤናና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ሲረጋገጥ ደግሞ በአገሪቱ ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

12.2.6. የዝርያ ለቀቃ ኮሚቴ ከማቋቋም ጀምሮ እስከ ለቀቃ ግምገማ ባለው ሂደት ውስጥ የሴቶችን አሳታፊነት እና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ እዲከናወን ይደረጋል።

## 13. የዕፅዋት ዝርያ አዳቃዮች እና የአርሶ /አርብቶአደሮች መብት ጥበቃ

ለብዙ ሺህ አመታት አርሶ/አርብቶ አደሮች የዕፅዋት ዘሮችን ለምግብ፣ ለመድሀኒትና ለጎጆ ኢንዱስትሪ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት ሲጠቀሙ፣ ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፉና መረጣ ሲያካሂዱ ኖረዋል። ይህም ለዛሬው የሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ እና መኖ ብዝሀ ዘር ተለያይነት (Variability) መነሻ ከመሆኑም በላይ የሰው ልጅ ዛሬ ለደረሰበት የዕፅዋት ማዳቀል ሳይንስ መሰረት ጥሏል።

የዕፅዋት ዝርያ አዳቃዮች መብት ማለት ላስመዘገቡት ዝርያ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚሰጣቸው የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ ነው። ይህ መብት የአርሶ /አርብቶአደሮች ወይም በአንድ ማህበረሰብ ስም የተመዘገበን ዝርያ ያካትታል። የብዛ ዘር ጥበቃ እና ልማዳዊ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የአርሶ /አርብቶአደሮች ወይም የአንድ ማህበረሰብ መብት ጥበቃ ማለት በስማቸው የተመዘገበ ዕውቀትና ብዛ-ዘር በሚያመላክተው የምስክር ወረቀት መሰረት ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበት ነው።

ዝርያ ማፍለቅ ብዙ ወጪ፣ ዕውቀትና ጊዜ የሚጠይቅ ስለሆነ ዝርያ አፍላቂዎች ያፈሰሱትን ገንዘብና ያጠፉትን ጊዜ ባክኖ እንዳይቀር ዋስትና ይፈልጋሉ። በዚህ ረገድ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ብዙ አገሮች እንደእነዚህ ዓይነት መብቶች የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ በማድረጋቸው ከብዛ-ዘር ሃብታቸው ተጠቃሚነታቸውን አስጠብቀዋል፡፡ ይህንን ዋስትና መስጠቱ ዝርያ አፍላቂዎችን ያበረታታል፡፡ በዘርፉ ኢንቨስትመንትም ያሳድጋል፡፡ በኢትዮጵያ ግን አተገባበሩ ምንም የለም በሚባል ደረጃ የሚገኝ ነው፡፡ በተጨማሪም የአርሶ/አርብቶ አደሮችና የማሕበረሰብ ዕውቀት መብት ጥበቃ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ከዚህም የተነሳ በዘርፉ የውጭ ኢንቨስትመንት የተዳከመ እንዲሆን፣ተወዳዳሪ የሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች ገበያ ውስጥ እንዳይገቡ እና የአርሶ/አርብቶ አደሩ ዕውቀትና ዘረ-መል ሃብት ለዝርፊያ እንዲጋለጥ ምክንያት ሆኖአል፡፡በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ተግዳሮቶች፣ ማነቆዎችና የፖሊሲ መፍትሄዎቻቸው ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

13.1. በዝርያ አዳቃዮችና በአርሶ/አርብቶ አደሮች መብት ጥበቃ የሚታዩ ተግዳሮቶች እና ማነቆዎች፡-

13.1.1. የአዳቃዩን የዕፅዋት ዝርያ ማፍለቅና ማጎልብት ተነሳሽነት ለማስቀጠል የሚያስችልና መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ የሚያበረታታ ሥርዓት አለመኖር፤

13.1.2. አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች በግል ወይም በማህበረሰብ ደረጃ በራሳቸው ተነሳሽነት እና ጥረት ለሚያሻሽሏቸው ሆነ ለዘመናት ለጠበቋቸው የሰብል ዝርያዎች የባላቤትነት ወይም የጥቅም ተጋሪ የሚያደርጋቸው ስርዓት ተግባራዊ ያለመሆን፤

13.2. መንግስት በዝርያ አዳቃዮችና አርሶ/ አርብቶ አደሮች መብት ጥበቃ ረገድ የሚታዩት ቁልፍ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ የሚከተሉትን የፖሊስ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

13.2.1. ቀጣይነት ያለው የዕፅዋት ዝርያ ማፍለቅ፣ ማጎልበት፣ማምረትና ማሰራጨት ለማበረታታት የሚያስችል የዝርያ ባለቤትነት (የአዳቃዮች መብት፣ የማኅበረሰብ ዕውቀትና መብት) አመዘጋገብና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት ይዘረጋል፤

13.2.2. አገሪቱ የዕፅዋት ዝርያዎች ለማመንጨት የሚውል ብዛዘር ተጠቃሚ እንድትሆን አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎችንና ስምምነቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፤



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

13.2.3. የአርሶ/አርብቶ አደሮች ዝርያዎች ምዝገባ ሥርዓት ከመደበኛው የዝርያ ባለቤትነት ምዝገባ ሥርዓት በተለየ መንገድ ይሰተናገዳል፤ ይህም በአካባቢ የተላመደ፤ ለዘመናት ተጠብቆ የቆየና ጠቀሜታዉ የተረጋገጠ የዕፅዋት ዘር የማህበረሰቡ ባለቤትነትና ሉአላዊነትን ባሰጠበቀ መልኩ ተመዝግቦ ጥቅም ላይ የሚዉልብት ስርዓት ይዘረጋል።

13.2.4. አርሶ/አርብቶ አደሮች ያመረቱትን እህል እንደ ዘር የመጠቀም ሉዓላዊ መብታቸው የሚከበር ይሆናል።

## 14. የዕፅዋት ዘር ማምረትና ማዘጋጀት

የዕፅዋት ዘር ማምረትና ማዘጋጀት ማለት ዝርያ ከተለቀቀ ወይም ከተመዘገበ በኃላ ከአራቢ ዘር እስከ የተመሰከረለት ዘር ያሉትን ትውልዶች ማባዛት፣ ማበጠር፣ ማሸት እና ማሸግ ያሉትን ተግባራት ያካትተል። ምርጥ ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ማቅረብ ብዙ ባለ ድርሻ አካላት የሚያሳትፍና የእነዚህን ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ሃላፊነት የተሞላበት አስተዋፅኦ እውን ማድረግን ይጠይቃል። በአገሪቱ እነዚህን አካላት አቀናጅቶ መምራትና ማስተባበር በአብዛኛው ያልተሳካ ተግባር ነው። ይህም በመሆኑ የመነሻ ዘርን በሚፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ ዓይነትና በፍትሃዊነት እንዳይቀርብ በማድረጉ አርሶና/አርብቶ አደሩም በፍላጎቱ መሰረት የተመሰከረለተ ዘር በጥራትና በመጠን እና በተፈለገው ጊዜ እንዳያገኝ ምክንያት ሆኖአል። ከዚህ አንፃር በአገሪቱ በዘር ማምረት የሚታዩ ቁልፍ ማነቆዎችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ቀጥለው ሰፍረዋል።

14.1. በዘር ማምረት የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች

14.1.1. በዘር ማምረት ሂደት የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች አስተዋፆ አነስተኛ መሆኑ፤

14.1.2. በሁሉም ዘር አምራቾች ዘንድም የኃላፊነትና ተጠያቂነት አሰራር የሌለና የዘር ማምረት ዕቅድም ትክክለኛ ፍላጎትን መሠረት ያላደረገ በቅንጅትም የማይከናወን መሆኑ፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

14.1.3. የመንግስት እና የግል ዘር አምራቾች ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው የሰብል ዝርያዎች ላይ ማተኮራቸው በአርሶ/አርብቶ አደሩ ተፈላጊ በሆኑ የሰብል ዝርያዎች የዘር አቅርቦት ክፍተት መፍጠሩ ፤

14.1.4. አምራቾች ለብዜት የሚሆን መነሻ ዘር እና በአጠቃላይ ለዘር ማምረት እና ማዘጋጀት የሚሆን ብድር በሚፈለገው መጠንና ዓይነት አለማግኘታቸው፤

14.1.5. የዘር አባዢዎች ለዘር ማባዣ የሚሆን የመስኖና የመኸር ማሳ እጥረት መኖሩን ተከትሎ ዘር በኮንትራት የሚባዛበትም ህጋዊ አሰራር ያልተዘረጋለት መሆኑ፤

14.1.6. በዘር ማምረት ሥራ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ ለመሰማራት መሬት እንደመስፈርት የሚጠይቅ አሠራር በመኖሩ የአምራቾች ተሳትፎ ዝቅተኛ ማድረጉ፤

14.1.7. ለምግብ ዋስትና በተመረጡ ሰብሎች ለችግር ወቅት የሚሆን የመጠባበቂያ የዘር ክምችት (strategic seed reserve) አሰራር አለመዘርጋቱ፤

14.1.8. በዘር ማምረት ስራ ላይ ለሚሰማሩ አካላት የኢንሹራንስ ስርዓት ያለመስፋፋቱ ፡፡

14.2. ዘር በማምረት የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶና ችግሮችን ለመፍታትት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፤

14.2.1. የውጭ እና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች እና አርሶ/አርብቶአደሮች በልዩ ልዩ መልኩ ራሳቸውን አደራጅተው በዘር ማምረት ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

14.2.2. የተለያዩ የዘር ትውልዶችን ኃላፊነት ወስደው ማባዛት ያለባቸው ተቋማት በማምረት ብቃት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያዎች መሠረት ይወሰናል፤

14.2.3. ዘር ማምረት ከመነሻ ዘር ጀምሮ ከትክክለኛ ፍላጎት በመነሳት በቅንጅት ታቅዶ እንዲመረት ይደረጋል፤

14.2.4. መንግስት ለዘር ማምረቻና ማበጠሪያ የሚያግዙ መሣሪያዎችን እንዲሁም ለዘር ማስመረቻና መግዣ የሚሆን የፋይናንስ ሥርዓት ያመቻቻል፣

14.2.5. ሥነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ ዘር ብዜትን ማካሄድ እንዲቻል መንግስት የመስኖ መሰረተ ልማቶችን ያጠናክራል፣ የዘር ማባዣ መሬቶችን ለአባዥዎች ያቀርባል፣

14.2.6. የመንግስት የዘር አምራች ድርጅቶች ውጤታማነታቸውን ለማሳደግ የግል ዘርፉ በከፊል የዕጣ ድርሻ እንዲኖረው ይደረጋል፤

14.2.7. ዘር በጥራትና በሚፈለገው መጠን እንዲመረት በውል ላይ የተመሰረተ የዘር ማምረት አሰራር እንዲጠናከር ይደራጋል፤

14.2.8. የሥነ-ምግብንና ምግብ ዋስትና፣ለኤክስፖርትና ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚሆን ምርት ማምረትን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸውን የሰብል ዝርያዎች በቀጣይነት እንዲመረቱ ለማድረግ መንግስት የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፤

14.2.9. የዕፅዋት ዘር አምራቾችን ከሰብል ምርት ውድቀት የሚታደግ የኢንሹራንስ አገልግሎት እና በዘር ማምረትና ዝግጅት ተግባር እንዲቆዩ የሚያበረታቱ ሌሎች ማትጊያዎች የሚያገኙበት የአሰራር ሥርዓት ይመቻቻል፤

14.2.10. የእፅዋት ዘር እጥረት በሚከሰትባቸው ዓመታት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ዘር ስትራቴጂክ በሆኑ ሥነምህዳሮች እንዲከማች የሚያስችል የእጽዋት ዘር መጠባበቂያ ክምችት ሥርዓት ይደራጃል፤

14.2.11. የመደበኛው የዘር ማምረት ለማያሟላቸው ዝርያዎች ዘር መንግስት በተሸጋጋሪና በኢ-መደበኛ የዘር ማምረት ሥርዓት እንዲሸፈን አስፈላጊው የድጋፍ ሥርዓት ይዘረጋል፤

14.2.12. የልውጥ ህያው ዝርያን ዘር ለማባዛት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

## 15. የዕጽዋት ዘር ግብይትና ሥርጭት

የዘር ግብይትና ሥርጭት ዋና ዓላማ ትክክለኛ የግብይት እና ሥርጭት ስርዓት በመዘርጋት አርሶ/ አርብቶ አደሩን የምርጥ ዘር ተጠቃሚ ለማድረግ እና የዘር አምራቾችና ነጋዴዎች የተለያዩ የግብይት መንገዶች (marketing channel) በመጠቀም የዘር አቅርቦትን ለማሳለጥና ውጤታማ ለማድረግ ነው፡፡ ውጤታማ የዘር ግብይትና ሥርጭት አለ ማለት የሚቻለው የዕጽዋት ዘር በሚፈለገው መጠን፣

በጥራት፣ በወቅታዊነት፣ በተወዳዳሪ ዋጋ እና ልዩ ልዩ የግብይት መንገዶች (marketing channel) ተግባራዊ በማድረግ የዘር ስርዓቱ የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው። የዘር ግብይትና ሥርጭት የራሱ ዋና ዋና ሂደቶች ያሉት ሲሆን የዘር ፍላጎት ዳሰሳ፣ የዘር አቅርቦት፣ ግብይትንና ሥርጭትን የሚያካትት ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ አገሮች የዘር ግብይትንና ሥርጭትን በሚመለከት በዋናነት በነፃ ገበያ የሚከናወን ሲሆን በተወሰነ መልኩ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መንግስትን በማሳተፍ የሚያካሂዱ የግብይትና ሥርጭት ተግባራት ተብለው ይታወቃሉ። በአገሪቱ ይህ በዋናነት በመንግሥት እየተከናወነ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ግን የቀጥታ ዘር ግብይት ሥርዓት እየተዘረጋ ይገኛል። ሆኖም ግን ውጤታማ የግብይት ሥርዓት ባለመኖሩ ምርጥ ዘር በዓይነት፣በመጠን እና በተፈለገው ጊዜ ባለመቅረቡ የአርሶአደሩን ፍላጎት ሳያሟላ በከፍተኛ መጠን በየአመቱ እያደረ ይገኛል። በአገሪቱ የዘር ግብይትና ሥርጭት የሚታዩት ቁልፍ ማነቆዎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

15.1. በዕፅዋት ዘር ግብይትና ስርጭት የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች

15.1.1. የዕፅዋት ዘር ፍላጎት ልየታ ሥርዓቱ ወቅታዊ፣ ገበያ ተኮርና የአርሶ/አርብቶ አደሩን ፍላጎት መሰረት ያላደረገና የፍላጎት መቀያየርን የማያስተናግድ መሆን፤

15.1.2. ቀደም ሲል ተለቀው ወደ ምርትና ግብይት ያልገቡትንና አዳዲስ የሚለቀቁትን ዝርያዎች ለተጠቃሚው የማስተዋወቅ ሥርዓት እና ተቋማዊ ቅንጅቱ የተጠናከረ አለመሆን፤

15.1.3. የአገሪቱ የዘር ግብይት መንግስት ተኮር፣ ተወዳዳሪነትን መሰረት ያላደረገ እና የግብይት ስትራቴጂን የማይከተል መሆኑ፤

15.1.4. በዘር ግብይትንና ሥርጭት ሥርዓት አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ የሆነ የክህሎት እና የአደረጃጀት ክፍተት መኖሩ ፣

15.1.5. የዘር ግብይትና ሥርጭት መረጃ ሥርዓቱ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ፤



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

15.2. በዘር ግብይት የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ችግሮችን ለመፍታት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል።

15.2.1. የመንግስት ዝርያዎች የመነሻ ዘር ሥርጭት በፍትሃዊነትና ውልን መሰረት ባደረገ መልኩ ለተመዘገቡ የመንግስትና የግል ዘር ድርጅቶች ተደራሽ ይሆናል፤

15.2.2. የዕፅዋት ዘር ግብይት በተወዳዳሪ የገበያ ሥርዓት እንዲመራና በዘር ግብይት ስትራቴጂ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን ይደረጋል፤

15.2.3. የአገሪቱ የዘር ግብይት ሥርዓት መንግስት ተኮር ከሆነው አብላጫ አሰራር ቀስ በቀስ ገበያ መር የሚሆንበት ሥርዓት ይዘረጋል፤

15.2.4. የሰብል ዝርያዎች እንደተለቀቁ ወዲያውኑ ምርምሩ፣ ኤክስቴንሽንና የግል ዘር አባዢ ድርጅቶች በቅንጅትና በስፋት በቅድመ ኤክስቴንሽን ሰርቶ ማሳያ አማካይነት እንዲያስተዋውቁ የአሰራር ሥርዓት እንዲጠናከር እንዲሁም ኃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር ይደረጋል፤

15.2.5. የተረጋጋ የዘር ግብይትን ለማስፈን የግብይት ሥርዓቱ ከዘር መጠባበቂያ ክምችትና ዘርን በአገር ወስጥና ለውጭ ገበያ ከመላክ ጋር የሚጣጣምበት የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

15.2.6. የዘር ምርት፣ ግብይት እና ስርጭት መረጃ መረብ በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲዘረጋ ይደረጋል፣

15.2.7. የዘር ግብይትንና ሥርጭት በመጠን፣ በጥራት፣ በወቅታዊነት እና በውድድር የተሻለ ሆኖ እንዲገኝ የተለያዩ የግብይት መንገዶችን (marketing channel) ለመጠቀም አማራጭ አሰራር ይዘረጋል፣

15.2.8. መንግስት ለአርሶአደሩ ቀረቤታ የሚኖራቸው የዘር መሸጫ ጣቢያዎች ዘር የሚፈልገውን ጥራት ጠብቀው አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊ የሆነውን መሰረተ ልማት እንዲስፋፋ ይደግፋል፤

15.2.9. የዘር ግብይቱ አርሶ/አርብቶአደሮችን እንደሚጎዳ ባረጋገጠበት ጊዜ ክፍተቱን ለመሙላት መንግስት አማራጭ አሰራሮችን ይዘረጋል።

15.2.10. በአርሶ/አርበቶ አደሩ የተመዘገበ ዘር በጥራት፣ በዓይነት፣ በመጠን በዘላቂነት ወደ ግብይት ስርዓቱ በማስገባትና የአርሶ/አርብቶ አደሩን የዕፅዋት ዘር ዋስትናና



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

ሉአላዊነትን ለማስከበር በሚያረጋግጥ መንገድ ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር ይዘረጋል፡፡

15.2.11.ሴቶች በዕጽዋት ዘር ግብይት ሂደት ሚና እንዲጫወቱ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው አሰራርና የልዩ ድጋፍ ሥርዓት ይረጋል፡፡

## 16. የዕፅዋት ዘር ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ስለ መላክ

ዘር ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ወደ ውጭ መላክ የሚቻለው በዋናነት ዓለም አቀፍ የጥራትና የጤና ደረጃዎችን ማሟላት ሲቻል ወይም የገዥውና የተቀባዩ አገር ፍላጎት ሲያሟላ ነው፡፡ ከሆርቲካልቸር ዘርና ለጥናትና ምርምር ተግባር ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡትና ከሚወጡት በስተቀር በአገሪቱ የሚታይ የዘር ኢምፖርት/ኤክስፖርት እንቅስቃሴ የለም፡፡ ሌሎች አገሮች በዘር ኢክስፖርት ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ የሚያገኙት ዘርፍ ሆኖአል፡፡ ኢትዮጵያ ግን በዚህ ረገድ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳታደርግ ቆይታለች፡፡ ከዚህም የተነሳ ካላት አቅም አንጻር ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ጥቅም እንዳታገኝ አድርጓታል፡፡ ስለዚህም ቀጥሎ በቀረቡት ማነቆዎች በመመስረት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተነድፈዋል፡፡

16.1.ዘር ወደ አገር ውስጥ በማስገባትና ወደ ውጭ በመላክ የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች፤

16.1.1. የአገሪቱ የዘር ሥርዓትና አቅም ያልዳበረ በመሆኑ ዘር ለውጭ ገበያ አቅዶ ማምረት አለመቻል፤

16.1.2. ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡት የአትክልት ዘሮች በስተቀር ከፍተኛ ምርታማነትና የጥራት ደረጃ ያለው ውጤት የሚያስገኙን በጣም ተፈላጊ ዝርያዎችን ዘር ወደ አገር ውስጥ ማስገባት አለመቻል፤

16.1.3. የውጭ የዘር ኩባንዎች ለሚያባዙት የዲቃይ ዘር ፤ ቅድመ መስራችና መስራች ዘሮችን በአገር ውስጥ ማባዛት ሲችሉ ከውጭ በማስገባታቸው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪ ማስከተሉ፤

16.1.4. በአገሪቱ የሚመረቱትን ዝርያዎች በውጭ ገበያ ያላቸውን ተፈላጊነት በማጥናት ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል ሥርዓት ያለመኖር፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

16.2. ዘርን ወደ አገር ውስጥ በማስገባትና ወደ ውጭ በመላክ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታትት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፡፡

16.2.1. ዘርን ወደ አገር ውስጥ በማስገባትና ወደ ውጭ በመላክ የሚሳተፉትን ለማበረታት መንግሥት ሁለተናዊ የአቅም ግንባታና የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፤

16.2.2. አገሪቱ የተቀበለቻቸውንና ዘር ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትና ወደ ውጭ ለመላክ የሚያበረታቱ አለምአቀፍ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ ስምምንነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፤

16.2.3. የውጭ ዘር ኩባንያዎች በአገር ውስጥ ያስመዘገቡአቸውን የድቃይ ዝርያዎችን ቅድመ መስራችና መስራች ዘሮችን በአገር ውስጥ የሚያባዙበት ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 17. የዕፅዋት ዘር ጥራትን ስለማረጋገጥ

ዘር ህይወት ያለው በመሆኑና የሚቀጥለውን ሰብል ትውልድ ውጤታማነት ስለሚወስን ዘርን በጥራት ማምረት፣ በአግባቡ መንከባከብና ከድህረ ምርት በኋላ በጥንቃቄ መጓጓዝ፣ መዘጋጀት፣ መከማቸትና መሰራጨት ይኖርበታል፡፡ የዘር ጥራትን ማረጋገጥ ማለት አንድ የተለቀቀና የተመዘገበን ዝርያ ከቅድመ መስራች እስከ ተመሰከረለት የዘር ትውልድ ድረስ የአገሪቱን የማሳና የቤተሙከራ የጥራት መስፈርቶችን አሟልቶ ስለመመረቱ ማረጋገጫ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡ ዘርን በጥራት የማምረት ተግባር የአምራቹ ኃላፊነት ሲሆን ይህንን ማረጋገጥ ደግሞ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት ተቋም ወይም አካል ኃላፊነት ነው፡፡ በአንዳንድ አገሮች የጥራት ማረጋገጥ ሂደት አገልግሎቶች ለሦስተኛ ወገን በማስተላለፍ የሚሠራ ሲሆን የመጨረሻ ማረጋገጥ ግን አግባብ ያለው የመንግሥት አካል ኃላፊነት ነው፡፡ ይሁንና በኢትዮጵያ እስካሁን እነዚህ ባለመተግበራቸው ደረጃውን የጠበቀ ጥራት ያለው ዘር ለተጠቃሚው ማቅረብ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ በቀረቡት ተግዳሮቶችና ማነቆዎች ላይ በመመስረት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተነድፈዋል፡፡



የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

17.1.በዕፅዋት ዘር ጥራት ማረጋገጥ የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች

17.1.1. የዘር ጥራት አረጋጋጭ አካላት በዘር እሴት ሰንሰለቱ የሚጠበቅባቸውን የዘር ጥራት የማረጋገጥ ሥራ የዘር ጥራት ፍተሻ ቤተ ሙከራዎችና ማዕከላትን በዕውቀት፣ በክህሎት እና በሙያ ስነ ምግባር በታነፀ የሰው ኃይል፣በሎጂስቲክስ እና ዘመኑ ባፈራው መሰረተ ልማት አደራጅቶ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት አለመቻል፤

17.1.2. አገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘር ጥራት ማረጋገጥ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በአባልነት ተሳታፊና ተጠቃሚ የምትሆንበት ሁኔታ አለመመቻቸት ቀጣይ በዘር ኤክስፖርት እንዳትሳተፍ የሚያደረግ መሆኑ፤

17.1.3. የዘር አምራቾች የተሟላ የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት በተደራጀ መልኩ የተጠናከረ አለመሆን፤

17.1.4. በዘር ጥራት ማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ለሚፈጠረው የጥራት መጓደል የተጠያቂነት አሰራር ተጠናክሮ አለመዘርጋት፤

17.2. በዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ችግሮችን ለመፍታትት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይከተላል።

17.2.1. የዕፅዋት ዘር ጥራት ማረጋገጥን የሚመሩ የክልል ተቋማት ራሳቸውን ችለው እንዲደራጁና የማስፈጸም አቅማቸውም እንዲጠናከር ይደረጋል፤

17.2.2. በዕውቀትና ክህሎት የታነፀ ባለሙያ፣ በዘመናዊ መሰረተ ልማት የተደራጀ፤ አለም አቀፍ ዕውቅና ያለው እና የክልል የዘር ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪዎችን የፍተሻ አፈጻጸም አቅም የሚደግፍ፣ የሚከታተልና የሚያረጋግጥ ተግባራትን የሚያከናውን ሪፈራል (Referal) ቤተ ሙከራ በፌደራል ደረጃ ይቋቋማል፤

17.2.3. በዕውቀትና ክህሎት የታነፀ ባለሙያ፣ በዘመናዊ መሰረተ ልማት እና ሎጂስቲክስ የተደራጀ የክልል የዘር ጥራት ፍተሻ ቤተ ሙከራዎችና ማዕከላት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፤

17.2.4. ዘር አምራቾች የተጠናከረ የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ይደርጋል፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

17.2.5. የመንግስት የዕጽዋት ዘር ጥራት ማረጋገጥ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት የሚሰጠውን አገልግሎት ለማቀላጠፍ በመስክም ሆነ በላቦራቶሪ የዘር ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት በግልም ሆነ በተደራጀ መልኩ መስጠት ለሚፈልጉ አካላት ድጋፍ ይሰጣል።

17.2.6. በዘር የእሴት ሰንሰለት የተሠማሩ ባለድርሻ አካላት የዘር ጥራት አረጋጋጭ አካላትን ጨምሮ በሚያከናውኗቸው የዘር ጥራት ጉድለቶች ላይ የሕግ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ይደረጋል።

## 18. የዕፅዋት ዘር ኳራንቲን

የዕፅዋት ኳራንቲን ማለት ዘርን ዕፅዋትን ከሚጎዱ ሕይወት ካላቸው ነገሮች ለመከላከል የሚደረግ የቁጥጥር ተግባር ነው። ቁጥጥሩ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ፣ወደ ውጭ በሚላኩ እና በአገር ውስጥ በሚዘዋወሩ ዕፅዋት፣የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር በሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ላይ ነው። የዕፅዋት ኳራንቲን አሠራር ዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፍ ተከትሎ የሚከናወን ቢሆንም አገሪቱ የዕፅዋት ዘር ኳራንቲንን አስመልክቶ ዓለም አቀፉን አሠራር ለማሟላት ሳትችል ቆይታለች። በመሆኑም በርካታ ባዕድ ጎጂ ተባዮች ወደ አገር ውሰጥ ገብተው በመስፋፋት ጉዳት በማድረስ ላይ ናቸው። በተጨማሪም ወደ ውጭ ለሚላኩ ምርቶች ደረጃውን የጠበቀ የኳራንቲን አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ የኤክስፖርት አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። ስለዚህም በአገሪቱ በሚታዩ ማነቆዎች በመመስረት የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተነድፈዋል።

18.1.በዘር ኳራንቲን የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች፡-

18.1.1. የዘር ጤንነት የሚረጋገጥበት አስፈላጊ የምርመራ ላቦራቶሪ በሰለጠነ ሰው ኃይልና መሰረተ ልማት አለመደራጀት፣ በሁለንተናዊ መልኩ አለመሟላትና አስተማማኝ የማረጋገጫ ሥራ መሥራት አለመቻል፤

18.1.2. ወደ አገር ውስጥ የገባን ዘር በኢንስፔክሽን ብቻ ተመሥርቶ ከመሠራጨቱ በፊት ለዚሁ ተብሎ በሚደራጅ ቦታ በማሳደግ ክትትል የሚደረግበት የድኅረ

መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) መሠረተ ልማት አለመኖር፤

18.1.3. አገሪቱ ሰፊ የየብስ አዋሳኝ ድንበር ያላት በመሆኑ ብዙ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤትና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተጠናከሩ በቂ የኳራንቲን ጣቢያዎች አለመኖር፤

18.1.4. የአገር ውስጥ ኳራንቲን ባለመቋቋማቸው ለተባዮች መስፋፋት ምክንያት መሆኑ፤

18.1.5. በዘር ኳራንቲን የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎችን ለመፍታት መንግሥት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይከተላል።

18.1.6. የኢንስፔክሽንና የምርመራ መሠረተ ልማቶች (Inspection and Testing Laboratories) በማሟላት የዘር ጤንነት ምርመራ እንዲጠናከር ይደረጋል፤

18.1.7. የድህረ መግባት ኳራንቲን አገልግሎት የሚሰጥባቸው መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉና ወደ ሥራ እንዲገቡ ይደረጋል፤

18.1.8. በየክልሎቹ የአገር ውስጥ ኳራንቲን አግልግሎት እንዲቋቋም፣ እንዲጠናከርና የሕግ ድጋፍም እንዲኖረው ይደረጋል፤

18.1.9. የኳራንቲን ጣቢያዎች ወሳኝ በሆኑ መግቢያ ቦታዎች በማቋቋም በቁጥር እንዲጨምሩ፤ በአቅምም እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

## 19. የዕፅዋት ዘር ብዝኃ ሕይወት

ብዝኃ ሕይወት ሲባል ሁሉንም ሕይወት ያላቸው ቁሳዊ ሀብቶች (ጀነቲክ ሀብቶች) የሚመለከት ነው፤ የዕፅዋት ብዝኃ ሕይወት ሲባል ግን የዕፅዋት ጀነቲክ ሀብትን ብቻ የሚመለከት ነው። ጀነቲክ ሀብት መጠበቅ፣ በቀጣይነት መጠቀምና ከጀነቲክ ሀብቱ መጠቀም ጋር የሚያያዝ የጥቅም ተጋሪነት ማረጋገጥ ዋነኞቹ የብዝኃ ሕይወት ዘርፉ ዓላማዎች ናቸው። እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በዕፅዋት ጀነቲክ ሃብት የታደሉ አገሮች ይህንን ሃብታቸውን በተገቢው ደረጃ በማንበር በመገምገም፣ በመመዝገብና በቀጣይነት ጥቅም ላይ እያዋሉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ አበረታች ተግባራት እያከናወነች ቢሆንም ገና ብዙ ይቀራታል።

የዕፅዋት ጀነቲክ ሃብቶች ለተለያየ ጥቅም ማለትም ለምርምር ለምርትና ፍጆታ ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ስለሚዘዋወሩ ለተባዮች መስፋፋት ዋና ምክንያት ሆኗል። በተጨማሪም የአገሪቱን ጀነቲክ ሃብት በመውስድ ጥቅም ላይ ካዋሉ አካላት የጥቅም ተጋሪነትዋን ማረጋገጥ አልቻለችም።

19.1.በአገሪቱ የዕፅዋት ዘር ብዝኃ ሕይወት የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች

19.1.1. መደበኛና ኢ-መደበኛ የዘር ሥርዓት (Formal and Informal Seed system) አቀናጅቶ አለመምራት የአገሪቱን የዕፅዋት ብዝኃ ሕይወት ሀብት በአግባቡ መጠበቅና መጠቀም አለማስቻሉ፤

19.1.2. ለመደበኛው የዘር ሥርዓት መነሻ የሆነን ብዛዘር ምንጭ የማሳወቂያው ሥርዓት አለመጠናከሩ የአርሶአደር ዝርያዎች፣ ዕውቀትና የማሕበረሰብ መብቶች ማስከበር አለመቻል፤

19.1.3. የአገሪቱን የዕፅዋት ዘር ብዝኃ ሕይወት ሃብት በመሰብሰብ፣ በማንበርና በመጠበቅ በኩል ያለው አቅም በሚፈለገው ደረጃ ላይ ባለመሆኑ ሃብቱ በብዝኃ ሕይወት ዘራፊዎች (Bio pirates) እየተመዘበረ መሆኑ፤

19.1.4. በዘረመል ምህንድስና (Genetic Engineering) የተገኘ ዘር በብዝኃ ሕይወት ላይ ሊያሳድር የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ማወቅ አለመቻል፤

19.1.5. አገር በቀል ብዛዘር በማሻሻል (Enhancement) ለዝርያ ማፍለቅና ማጎልበት ተግባር እንዲውሉ የሚያስችል አሰራር ውስን መሆን፤

19.2. በዕጽዋት ዘር ብዝኃ ሕይወት የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች ለመፍታት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይከተላል፤

19.2.1. አዳቃዮች ዝርያ ሲያፈልቁ እና ሲያድሱ የብዛዘር ምንጩ እንዲታወቅ የሚያደርግ ሥርዓት (Traceability Mechanism) እንዲጠናከር ይደረጋል፤

19.2.2. የመደበኛውና መደበኛ ያልሆነው የዘር ሥርዓት እርስ በራሳቸው እየተመጋገቡ ዘላቂ ዕድገት የሚያስመዘግቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

19.2.3. አገሪቱ የፈረመቻቸውን የብዝኃ ሕይወት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲከበሩ ይደረጋል፤

19.2.4. የአገር በቀል ብዝሀ ዘር ለዝርያ ማፍለቅና ማሻሻል ተግባር እንዲውል የሚያስችል የተሻለ አሰራር ይዘረጋል፤

19.2.5. የተለያዩ የባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎች ለዝርያ ማፍለቅ፣ ልየታና ማሻሻል ጠቃሚነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ደህንነትን በማረጋገጥ በዘረመል ምህንድስና ረገድ አቅም የመገንባትና ተጠቃሚነትን የማስፋፋት ሥራ በትኩረት ይሰራል።

## 20. የዕፅዋት ዘር ሥርዓት አደረጃጀት እና አመራር

የዕፅዋት ዘር ዘርፍ ከአንድ ሴክተር እና ከአንድ ተቋም በላይ ሽፋን ያለው ዘርፍ ነው። ስለሆነም አመራሩ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ተሳትፎና ኃላፊነት የሚጠይቅ ነው። በአገሪቱ የዘር አመራር ማዕቀፍ በፌደራልና በክልል መንግሥታት ኃላፊነት ሥር ያለ ቢሆንም ፖሊሲዎችና ሕጎች ለመተግበር የሚያስችል ተገቢ የአመራር ሥርዓት (seed governace) ግን እስከአሁን አልተዘረጋም። በአሁኑ ጊዜ ዘርፉ እንዲያድግና እንዲሻሻል ከምንጊዜም በላይ ስትራቴጂካዊ አመራርና አቅጣጫ የሚሰጥ አካል መኖር አስፈላጊነቱ የላቀ ቢሆንም ይህ ግን በአሁኑ ጊዜ ተሟልቶ አይገኝም።

20.1. በዕፅዋት ዘር ሥርዓት አደረጃጀት አመራር የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች

20.1.1. የዕፅዋት ዘር ሥርዓቱን በበላይነት የሚመራ ብቃትና ተጠያቂነት ያለው አደረጃጀት በተጠናከረ መልኩ አለመኖር፤

20.1.2. በዝርያ እና በዘር ትውልድ መተካካት ላይ የተመሰረተ የተቀናጀ ስትራቴጂካዊና አገራዊ የዘር ብዜት የዕቅድ ስርዓት በተጠናከረ ሁኔታ አለመኖር፤

20.1.3. የሕግ ማዕቀፎችንና የስትራቴጂዎችን አፈጻጸም መከታተል፣መደገፍና መገምገም አለማስቻል፤

20.2. በአደረጃጀት እና አመራር የሚታዩ ቁልፍ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች ለመፍታት መንግስት የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይከተላል፤

20.2.1. የዘር ዘርፉን የእሴት ሰንሰለት ተዋናዮች በተቀናጀ፣ በብቃትና በተጠያቂነት የሚመራ አደረጃጀት ይዘረጋል፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Agriculture

20.2.2. በፌደራል ደረጃ የዝርያ ለቀቃና ምዝገባ፣ የዝርያ መብት ጥበቃ፣ የዘር ጥራት ማረጋገጥና ኳራንቲንን በተመለከተ በአገር ደረጃ በተቀላጠፈ መልኩ አገልግሎት የሚሰጥ በአንጻራዊ መልኩ ራሱን ችሎ የሚወስን መንግስታዊ ተቋም ሆኖ እንዲደራጅ ይደረጋል፤

20.2.3. በክልል ደረጃ የዘር ጥራት ማረጋገጥንና ኳራንቲን አገልግሎትን ሊመራ የሚችል መንግስታዊ ተቋም በብቁ የሰው ኃይል እንዲደራጅና በአንጻራዊ መልኩ ራሱን ችሎ የሚወስን አካል ሆኖ እንዲሠራ ይደረጋል፤

20.2.4. የዘር አመራር፣ አስተዳደርና አደረጃጀት የሚሰጠው አገልግሎት ብቃት ለማረጋገጥ በአስፈላጊ ጊዜ የአመራርና አደረጃጀት ግምገማ በማካሄድ ወቅታዊ ማሻሻያዎች እንዲወሰዱበት ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ልዩ ልዩ ጉዳዮች

## 21. የፖሊሲው አጭር መግለጫ

የዕፅዋት ዘር ፖሊሲ የሚመነጨው ከግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሆኖ ፖሊሲው ጥቅል በመሆኑ የዕፅዋት ዘር ዝርዝር ፖሊሲ በማውጣት ኢንዱስትሪውን በዓለም ተወዳዳሪ በማድረግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ፍላጎት ለማሟላት፤ በዓለም አቀፍም ተወዳዳሪ በማድረግ ለውጭ ምንዛሪ ግኝት አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ማስቻል ነው፡፡

## 22. የፖሊሲ ክትትል፣ የግምገማና የክለሳ ስርዓት

በፖሊሲው ትግበራ ሂደት አስፈላጊ ክትትልና ግምገማ በማድረግ መረጃዎች ይሰሰባሉ፡፡ መረጃዎችን በመተንተን ለፖሊሲው አፈፃፀም እንቅፋት የሆኑትን እና አገራዊና ዓለም አቀፋዊ እድገትን ተከትሎ የሚመጡ አዳዲስ አሰራሮችን በመለየት ፖሊሲው እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 23. የፖሊሲው ስርጭት

የፀደቀው የፖሊሲ ሰነድ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ጉዳዩ ስሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## 24. ፖሊሲው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውክልና በግብርና ሚኒስቴር ማናጅመንት ከፀደቀበት ከየካቲት/2012 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ዕዝል አንድ፡- የቃላትና ፅንሰ ሀሳብ ፍቺ

በዚህ ፖሊሲ መሰረት፡-

፩/ ዘር ማለት ለዕፅዋት ማራባት የሚውል ዕውን ዘር፣ አኩራች፣ የተክል ቁርጥራጭ፣ ስራ ስር፣ ችግኝ ወይም ማንኛውም የተክል አካል ነው፡፡

፪/ የዘር ትውልድ ማለት የአንድ ዝርያ እናት፣ አራቢ፣ ቅድመ መስራች፣ መስራችና የተመሰከረለት ዘር ሰንሰለትን የሚያጠቃልል ደረጃ ነው፡፡

፫/ አራቢ ዘር ማለት የዝርያው ባለቤት ወይም ወኪሉ በቀጥታ እየተቆጣጠረው የሚባዛና የሚቀርብ የመጀመሪያው የዘር ትውልድ ደረጃ ነው፡፡

፬/ ቅድመ መስራች ማለት ከአራቢ ዘር የሚቀጥል የዘር ትውልድ ደረጃ ነው፡፡

፭/ መስራች ማለት ከቅድመ መስራች የሚቀጥል የዘር ትውልድ ደረጃ ነው፡፡

፮/ የተመሰከረለት ዘር ማለት በትውልዱ ከመስራች ዘር የሚቀጥል የዘር ትውልድ ወይም ከመስራች ዘር ከሚገኘው ከአንደኛው፣ ሁለተኛው ወይም ሶስተኛው የዘር ደረጃ የሚገኝ ነው፡፡

፯/ ልውጥ ህያው ማለት ሰው ሰራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ህያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረ መል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ስለተከተተበት የዘረ መሎች ይዘቱ ወይም የባህሪው ክስተት የተለወጠበት ህያው ነው፡፡

፰/ የጥራት ቁጥጥር ማለት አንድ ዘር የኢትዮጵያን የዘር ደረጃ መስፈርት ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚከናወን የቁጥጥር ሂደት ነው፡፡

፱/ ዝርያ ማለት በአንድ ዕፅዋት ቤተሰብ ውስጥ የታወቀ ዝቅተኛው ደረጃ ሆኖ፡

ሀ/ ከአንድ ተወሰነ ጂኖታይፕ ወይም ከብዙ ጂኒታይፖች ጥምረት የሚመነጩ ባህርያትን የሚገልፅ፤

ለ/ ካሉት ባህርያት ቢያንስ በአንዱ ከማንኛውም ዕፅዋት ስብስቦች የሚለይ እና

ሐ/ ባህርያቱን ሳይቀይር መራባት በመቻሉ ምክንያት እንደ አንድ አይነት ሊወሰድ የሚችል የዕፅዋት ስብስብ ነው፡፡

፲/ ዝርያ መልቀቅ ማለት የተመዘገበው ዝርያ ለአገር ውስጥ ገበያ እንዲባዛ፣ እንዲመረት ወይም ዘሩ ለሽያጭ እንዲውል መፍቀድ ነው፡፡

፲፩/ አዳቃይ ማለት ዝርያ የሚያዳቅል በለሙያ ማለት ነው፡፡

፲፪/ የዘር ኢንዱስትሪ ማለት ብዝሀ ዘርን ተጠቅሞ ዝርያ ማፍለቅን፣ ዝርያ ማስመዝገብን፣ ዘር ማባዛትን፣ ማዘጋጀትን፣ ግብይትን፣ ዘር ወደ ውጭ መላክንና ማስገባትን፣ የጥራት ቁጥጥርን እና በዘር እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚጠቃለሉ ሂደቶችን የሚሸፍን የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው፡፡

፲፫/ የዘር ስርዓት ማለት ከዝርያ ማፍለቅ እስከ ዘር ግብይት እና ስርጭት ያለው የእሴት ሰንሰለት ነው ፡፡

፲፬/ የዝርያ አፅዳቂ ኮሚቴ ማለት ባለድርሻዎችን በእኩልነት ሊያስተዳድር በሚችል ራሱን ችሎ በተደራጀ መንግስታዊ ተቋም የሚሰየምና ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጣ በየአመቱ የሚቀርቡለትን ዕጩ ዝርያዎች የመመዝገብ ጥያቄዎችን የሚገመግም አካል ነው፡፡

፲፭/ ዝርያ ማደስ ማለት አንድ የዕፅዋት ዝርያ ሲመዘገብ የነበረውን የአግሮኖሚና የጥራት ባህርያት ከትውልድ ትውልድ ይዞ ይገኝ ዘንድ በየጊዜው ከበሽታ፣ ከጀነቲክ እና ማንኛውም መደበላለቅ ነፃ ሆኖ ይቀጥል ዘንድ የሚደረግለት እንክብካቤ ነው፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ... The Federal Democratic Republic of Ethiopia ... Agriculture

፲፮/ ብዝሀ ዘር ማለት በአንድ አይነቱ (Species) ውስጥ በሰው ሰራሽ ሳይሆን በተፈጥሮ ሰፊ ተለያይነት ያለውና በውስጡ ብዙ ጠቃሚ የአግሮኖሚ ባህርያትና ዘረ መሎችን የያዘ ዘር ነው ።

፲፯/ የዝርያ ማዳቀል ማለት በአንድ የዕፅዋት አይነቱ (Species) ውስጥ በብዝሀ ዘር ወይል ሌሎች ዝርያዎች ውስጥ ያሉ ጠቃሚ ባህርትን ወደ አንድ ድቃይ ለማምጣትና ዝርያን ለማፍለቅ የሚደረግ ሳይንሳዊ ሂደት ነው።

፲፰/ ዝርያ ማፍለቅ፡ ማለት በማዳቀልና መረጣ ዘዴዎችን በመጠቀም አዲስ ዝርያ ማፍለቅ ነው።

፲፱/ የዘር ሉአላዊነት ማለት የራስህን ዘር የመጠቀም መብት ማለት ነው ።

፳/ ዘር ማዘጋጀት ማለት ዘር ማምረትን፤ ማበጠር፣ በፀረ ተባና በሽታ ማሸት፣ ማሸግና ማከማቸት የሚያጠቃልል ሂደት ነው።

፳፩/ የዕፅዋት ኳራንቲን ማለት አረም፣ ተባይ፣ በሽታ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ ወይም በአገር ውስጥ ከተከሰተ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይሰራጭ መቆጣጠር፤ ሲከሰትም ገድቦ መያዝ፣ ማውደም ወዘተ ማለት ነው።

፳፪/ የዕፅዋት ዘር ተጠቃሚ፡ ማለት አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደርና አልሚ ባለሀብትንና ማንኛውም የተሻሻለ ዘር ተጠቃሚ አካል ነው።

፳፫/ የምግብ ዋስትና በዚህ ፖሊሲ የስነ ምግብ ዋስትናንም ያካትታል።